# አንፀባራቂው ህዳሴ ያስደነበራቸው
# ሚርተኞቹና ቅዥታቸው

**በሰለሞን አጎናፍር**

ይወነጃጀላሉ፣ ይዘላለፋሉ፣ ይረጋገማሉ፣ ይወቃቀሳሉ፣ አንዳንዴም ሲበረታ በቦክስ ይቦቃቀሳሉ። የአገሬ ሰው "መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ" እንደሚለው ሆኖባቸው ተግባርና አላማቸው የሰማይና የምድር ያህል ተራርቆና የማይገናኙ ሆነው ሳለ እንደተቀናጁ ነግረውን ስማቸውንም ከዚሁ ተነስተው ይሰይማሉ።

ለአንድ ሴኮንድ አንድ ሆነው የማያውቁትን "አንድነት" ብላችሁ ጥሩን ይሉናል።ይህንን ሰምተን ሳንጨረስ እውነተኛውና የመጀመሪያው "አረንጓዴ" የተሰኘው ፓርቲ (የቀለም አይነቶችን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች በአብነት መጠቀም የጀመርኩት ሰማያዊ የሚባል ፓርቲ በቅርቡ በመመስረቱ እንደሆነ ይታወቅልኝ) "በፕሮፌሰር እከሌ----" የሚመራው ነው ይሉናል። እሺ ብለን ስንቀበል "በዶክተር እከሌ -" የሚመራው "ፎርጅዱ" በመሆኑ ወደዚያ እንዳትሄዱ ይሉናል ።ይሄኛውንም እሺ ብለን ስንቀበል "በአቶ እከሌ--- " የሚመራው ደግሞ ህገ ደንብ ጥሶ ከፓርቲው ከተባረረ በሁዋላ ያቋቋመው ፓርቲ በመሆኑ ወደዚያም አትሂዱ እንዳትሸወዱ ይሉናል።

የትኛውን እንመን? "የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል-" እንደሚለው የአገሬ ሰው ለአንድ አላማ ቆመናል እያሉ እርስ በእርሳቸውም የማይተማመኑና በጥርጣሬ የሚተያዩ ናቸው።

በአገሪቱ የሚካሄድ የአገር አቀፍም ሆነ የአካባቢ ምርጫ ከሌለ በስተቀር ከሁለትና ከሶስት አመት አንዴ ብቻ በሚገናኙበት ጉባኤና ስብሰባቸው በሃሳብ መግባባት እየተሳናቸው በቦክስ መቦቃቀሳቸው አልበቃ ብሎ በነፍስ ጭምር አንዱ በአንዱ ላይ በመዛት ይፈላለጋሉ።

እንዲህ ሲናቆሩና ሲታመሱ የሚታወቁት እነዚህ ሃይሎች ሲሻቸው ሰላማዊ ሲፈልጉ ደግሞ አመፅ አውርድን እንደልባቸው በየሚዲያው እየሰበኩ እንዲንቀሳቀሱና የተቃዋሚ ፓርቲ በሚል ሽፋን እንዲደራጁ ባስቻለ ህገ መንግስት የሚመራን መንግስት በፀረ ዴሞክራሲያዊነት ሲወቅሱ ስናይ የእራሳቸውን ትልቅ ግንድ መመልከት ባለመቻላቸው በእጅጉ እናዝናለን።

የ"ሚርተኞቹ" ድርጅትም ሆነ ፓርቲ የሚመራበት "መርህ" እና "ፕሮግራም" የሌለው ከመሆኑ በተጨማሪ አባላቶቻቸው የሚገዙበት የውስጥ ዴሞክራሲ መርህ እንደሌላቸው ቦክስ መቧቀሳቸው አፍ አውጥቶ ያሳብቅባቸዋል።

አንድ መሆናቸውን ለህዝብ በነገሩበት አንደበታቸው እንደ መስቀል ወፍ ከስንት አንዴ ወደ አደባባይ መግለጫ ለመስጠት ብቅ ሲሉ አንደኛው ማንበብ የጀመረውን መግለጫ "እንዴት እኛ ያላመንበትን መግለጫ የሁላችንም አስመስለህ ታቀርባለህ? በሚል ሌላኛው ሲያስቆመው በቴሌቪዥን የተመለከተው ኢትዮጵያዊ አፍሮባቸዋል። ተሸማቆባቸዋል።

መላው ዜጋ እነዚህ ሃይሎች በአደባባይ የሚሰብኩት ሌላ በተጨባጭ የሚገኙበት ሁኔታ ሌላ መሆኑን ከተገነዘበና ካወቀ ጥቂት የማይባሉ ጊዜያትን አስቆጥሯል። ከኢትዮጵያዊነት ስነ ምግባር ያፈነገጠ ስብእናቸውና ድርጊታቸው አገር ለመምራት ቀርቶ ኢትዮጵያዊ የሚለውን ባለ ግርማ ሞገስ የዜግነት ክብር ይዘው እንዲቀጥሉ ሊያደርጋቸው እንደማይገባ የተገነዘበው የኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይ ተስፋ ቆርጦባቸዋል።

እነርሱ ግን ይህ ሁኔታ  ቅንጣት ታህል ሳያሳፍራቸው ለመግለጫ በቀረቡበት የስብሰባ አዳራሽ "አንተ ተዋናይ እንጂ ማን ነው ደግሞ ፖለቲከኛ ያደረገህ? እየተባባሉ በተዘላለፉበት መገናኛ ብዙሃን ቀርበው ህዝቡን በይፋ እንኳን ይቅርታ ለመጠየቅ ያልታደሉ ሞራለ ቢስ ናቸው።

በአንድ ጉባኤ ላይ አንድ አቋም መድረስ አቅቷቸው የወጉን በአንድ ርእሰ ጉዳይ  ላይ መግለጫ ለመስጠት መገናኛ ብዙሃን ጠርተው በአባላቶቻቸው ቁጥር ልክ አንድ መቶ መግለጫ ማውጣት ሲያምራቸው የተመለከታቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ስማቸውን አይቶ ከእውነት ጋር በማይተዋወቀው ግለ ስብእናቸው ታዞባቸዋል። ሆደ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ።

መገናኛ ብዙሃንም በፓርቲው አመራሮች ዘንድ አንድ አቋም ያልተደረሰበትን የፕሬስ መግለጫ ይዘው ሽፋን ሊሰጡትም ሊተውትም ሲቸገሩ ያስተዋልንበት ጊዜያት በርካታ ናቸው።

በተለይ የህዝብ መገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞች ከሆኑ የፕሬስ መግለጫውን ባያስተናግዱት እናንተ የገዥው ፓርቲ መግለጫ ሲሆን እንጂ ወትሮስ ለእኛ ሲሆን እንዲህ አደላችሁ ይሏቸዋል። ይህንን ወቀሳ ፈርተው ሊያስተናግዱ ሲሞክሩ ደግሞ ይህ መግለጫ የፓርቲው አባላት ሙሉ ስምምነት የተደረሰበት ሳይሆን መርህ ይከበር በሚል የሚንቀሳቀሱትና የአፈንጋጮች በመሆኑ አድልዎ እንዳትፈፅሙ የሚሉና መሰል እነርሱ በቀን ቃኘርተው ሌላውም ግራ እንዲጋባ የሚያደርጉ አቋም ያራምዳሉ።

ይህን መሰል ክስተት አንድ ወቅት ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ እያጋጠማቸው ጋዜጠኞች ይህንና ለመሳሰሉ የፕሬስ መግለጫዎች በአንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲጠሩ በምን አግባብ ለአየር እንደሚያበቁት ሲቸገሩና ሲጨነቁ ያስተዋልንበት ጊዜ ጥቂት የሚባል አይደለም።

በሰላም የሚታገል፣ ለዜጎች የዴሞክራሲ መብት መከበር በብርቱ የሚተጋ፣ አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲ ማየት የማይጠላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን መሰል ቢያንስ ለእውነት መርህ መጠበቅ የማይቆም፣ ፀረ ዴሞክራትና አምባገነን ባህሪ ያላቸው ግለሰቦች ስብስቦች መደበቂያ የሆነ ፓርቲ "ተቃዋሚ" በሚል ሽፋን እንደ አሸን ቢፈላ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን ይፈይድለታል?

እንደ አሜባ ከአርባና ከአምሳ ቦታ እየተበጣጠሱና "መርህን እየጣሱ" ግን ደግሞ "ለመርህ ቆመናል" የሚሉት እነዚህ ሚርተኞች በዚህ ዘመን ከእነርሱ ስንትና ስንት እጥፍ በአስተሳሰብ የመጠቀውን የኢትዮጵያ ህዝብ እናሞኛለን ብለው ካሰቡ በቅድሚያ  የነፈዙት እነርሱ መሆናቸውን ሊገነዘቡ ይገባል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት ሃያ አንድ አመታት በዚህች አገር የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች በጉያቸው ጩቤያቸውን ደብቀው ከተቀናጁ በሁዋላ ሁለት አመት እንደተቀናጁ ሳይቀጥሉ ሲበታተኑ በእጅጉ ታዝቧቸዋልና።

እነዚህ የአመፅ ሃይሎች በመላው አገሪቱ ከአመታት በፊት የተካሄደውን ያለፈውን የምርጫ ውጤት አሸንፈው ኢትዮጵያን የመሰለ የበርካታ ብሄር ብሄረሰቦችና የተለያዩ እምነት ተከታዮች የሆነ አገር የመምራት ሃላፊነት ቢያገኙስ እንዲህ እየተጣሉና እየተነካከሱ ነበር የሚመሯት ብሎም ኢትዮጵያን ከእነርሱ የታደጋትን አምላክ ህዝቡ አመስግኗል።

ሟርተኞቹ "አማተር ፖለቲከኞቹ" በውስጠ ዴሞክራሲ ባህልና እሴት አባሎቻቸውን የማይመሩ ከመሆናቸውም በላይ ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚመኙት መንገድና የሚከተሉትና የሚመርጡት የትግል ስልትም በተመሳሳይ የሰላሙን ሳይሆን የአመፅና የብጥብጡን ነው።

በአገሪቱ የምርጫ ወቅት ካልሆነ በስተቀር "እንታገልለታለን" ከሚሉት ህዝብ ጋር ተገናኝተው የማያውቁት እነዚህ ፀረ ሰላም ሃይሎች በሁለት ሶስት አመት ጊዜ ውስጥ በሚያካሂዱት ጉባኤ ወይም ስብሰባ ላይም የሚመክሩት አሊያም የሚበጣበጡት ለህዝብ በሚጠቅም አጀንዳ ላይ ሳይሆን ከለጋሾቻቸው የተገኘውን ቢዝነስ በሚጠቀሙበት ሁኔታ ላይ ነው።

የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ የመሰረቱት የስልጣን ጥማቸው የማርካት ዋና ግባቸውን ለማሳካትና ፖለቲካን እንደ ቢዝነስ በማድረጋቸው እንጂ የህዝብ ብሶት ወይም ቅሬታ አንግብግቧቸው ቢሆን ኖሮ ቢያንስ ለዚሁ አላማ ውድ የሆነባቸውን መስዋእት እንዲያደርጉ ባይጠበቅም የህዝቡን አንገት በሚያስደፉ ተግባር ላይ ግን አይሰማሩም ነበር።

ብቻ ሟርተኞቹ በዚህች ኢትዮጵያችን ምድር ባለፉት ሃያ አንድ አመታት የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ጉዞ ሂደት ያላሳዩን ተውኔትና ድራማ የለም።

ሟርተኞቹ በዚህ መልኩ እየተተራመሱ ይቀጥሉ እንጂ ኢትዮጵያ ግን እድሜ ለህዝቦቿና ለመንግስት የጀመረችውን የህዳሴ ጉዞ ለአፍታም ላታቆም ቀጥላበታለች ።ፈጣን ለውጧ አለምን እያስደመመ የሚገኘው ይህች አገር ህብረ ብሄር ዜጎቿን በህብረት በማስተሳሰር የጀመረችው ጉዞዋ ምንም ምድራዊ ሃይል በማያደናቅፈው ሁኔታ በእርግጥም ሰምሮላታል።

በአስራዎቹ በሚቆጠሩ አመታት መካከለኛ ገቢ ወዳላቸው አገራት ተርታ ለመቀላቀል የሰነቀችው ጉዞ ስኬት የሚያበስሩ ድሎችም መመዝገብ ጀምረዋል።

ይህ ሁኔታም የፈጠረባቸውን አግራሞት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያን የመጎብኘት እድል ያገኙ የአለም ዓቀፍ መገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞች፣የተለያዩ አገራት መሪዎችና የአለም ታዋቂ ሰዎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እንዲገለፁት አድርጓቸዋል ።

ሟርተኞቹ ያሉትን ይበሉ እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ በአካል ተገኝቶ በኢኮኖሚው በግብርናው በጤናው በፖለቲካው በአጠቃላይ በሁሉም ነገር የሚታየው እድገትና መሻሻል አስደናቂ የሚባል መሆኑን ከሁለት ወራት በፊት ኢትዮጵያን የመጎብኘት እድል አግኝቶ የነበረው እውቁ የኮምፒዩተር ፕሮግራመር እና የአለማችን ቢሊዮነር ቢል ጌትስ ፅሁፍ በአይጋ ፎረም ድረ ገፅ ላይ ሰፍሮ ከጥቂት ቀናት በፊት አንብቤያለሁ። ይህንን ለአብነት መጥቀሱም ለአባባሌ ጥሩ ማሳያ በመሆኑ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ።

ቢል ጌትስ "Ethiopia's exciting innovation in Agriculture and health" በሚለው ፅሁፉ ወደ አፍሪካ በርካታ ጉዞዎችን ባደርግም በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ያደረኩት ግን በጣም አስደሳችና ለየት ይላል ነበር ያለው።

"ኢትዮጵያ በአንድ ወቅት የነበረችበት ድህነት እጅግ የከፋ ስለነበር ህዝቦቿን ለመመገብና ለእናቶችና ለህፃናት የጤና አገልግሎት ለመስጠት በማትችልበት ከፍተኛ ፈተና ውስጥ ወድቃ እንደነበር አስታውሳለሁ ያለው አሜሪካዊው ቢሊየነር ሆኖም በአሁኑ ወቅት ግን አገሪቱ በጤናው እና በግብርናው ዘርፍ ያመጣችው ከፍተኛ ለውጥና መሻሻል በእጅጉ አስደስቶኛል" ሲልም አስፍሯል።

ቢልጌትስ አያይዞም ኢትዮጵያ በጤናው ዘርፍ ለእያንዳንዱ ግለሰብ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት ተደራሽ በማድረግ ተምሳሌት የሚሆን ተግባር አከናውናለች ይላል።

በአገሪቱ በግብርናውና በጤናው ዘርፍ ይህን መሰል ከፍተኛ ለውጥ እንዲመጣ ቁልፍ አሰተዋፅኦ ያበረከተው ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና የመንግስታቸው የአመራር ብቃት ነው ሲልም በአፅንኦት ገልጿል፡፡

በየትኛውም አገራት በግብርናና በጤናው ዘርፍ ለውጦችን ለማምጣት ለመንግስታት ከፍተኛ ፈተና እንደሆነ ያመለከተው የቢልጌትስ ፅሁፍ ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ያሳየችውን ለውጥና እድገት አስደናቂ የሚያደርገውም ይኸው ሚስጥር ነው ሲልም አስረድቷል፡፡

አያይዞም እኛን ጨምሮ ሌሎች በኢትዮጵያ በጤና እና በግብርና ዘርፍ ለሚካሄዱ ተግባራት የገንዘብ ልገሳ ያደረጉ ለጋሾች እስካሁን የሰጡት ድጋፍ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ጥቅም እየሰጠ ያለ ትልቅ ኢንቨስትመንት እየተካሄደበት እንዳለ ሊገነዘቡ ይገባል ሲልም አመልክቷል።

እነዚህ በቢልጌትስ ፋውንዴሽናችን ቅድሚያ የተሰጣቸው ዘርፎች ስኬታማ መሆን ከቻሉ በዘርፎቹ ተመሳሳይ ተግዳሮቶች ባሉባቸው ሌሎች የአፍሪካ አገራት ተመሳሳይ ውጤት ለማስመዝገብ ኢትዮጵያን እንደ ሞዴል ሊወሰዱ ይገባል ሲል ገልፆ ይህም ተስፋዬን አለምልሞታል ብሏል ቢልጌትስ።

በኢትጵያ እየታዬ ያለው ለውጥና መሻሻል ቀደም ሲል ቢልጌትስ በገለፃቸው ሁለት መስኮች ብቻ የተወሰነ እንዳልሆኑ ሁለተኛ አብነት ላክል።

ባለፈው ሳምንት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ ዳይሬክተር ጆን ጊንግ ኢትዮጵያን ጎብኝተው ነበር።

እኝሁ የድርጅቱ ከፍተኛ ባለስልጣን ከጉብኝታቸው በሁዋላ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዜና ማእከል የኢትዮጵያን ጎብኝታቸውን አስመልክተው በሰጡት ቃለ ምልልስ የኢትዮጵያ መንግሥት እየጨመረ የመጣውን የአየር ንብረት ለመቋቋም የወሰደው ፈጠራ የታከለበት ውጤታማና ጠንካራ ጥረት እንዲሁም በምግብ ራስን የመቻል እርምጃን በይፋ አወድሰዋል።

ዳይሬክተሩ አያይዘውም “ኢትዮጵያ ድርቅን በመግታት ረገድ ተጨባጭ እመርታዎችን አሳይታለች” ማለታቸውን የዜና ማእከሉ ጠቅሶ “በኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት በሴፍቲኔት፣ በጤናና የተመጣጠነ ምግብ በማዳረስ ረገድ የተደረጉ ጥረቶች የበርካቶችን ሕይወት ታድገዋል፣ሚሊዮኖችን በአፍሪካ ቀንድ ከተከሰተው ርሃብም ማትረፍ ችለዋል” እንዳሉትም አመልክቷል።

እኚሁ ባለስልጣን “የኢትዮጵያ መንግሥት ተግባራዊ ያደረጋቸው ስኬታማ ፖሊሲዎች በአፍሪካ ቀንድ ብቻ ሳይሆን ድርቅ ባጠቃው የሳህራ በታች አካባቢ ላሉ አገራት ጥሩ ልምዶችን የሚሰጥ ነው” ማለታቸውንም ጠቅሷል።

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ መንግስታዊ ስልጣን ላይ ያለው ኢህአዴግ ቀደም ሲል በነበረው ታሪኩም ሆነ የዛሬ ተግባሩ ማጠንጠኛ ማእከል ኢትዮጵያ ለዘመናት ትታወቅበት ከነበረው የድህነት ታሪክ በማላቀቅ በቅርብ አመታት ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ማሰለፍ ነው።

በመሆኑም መንግስት ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለው መጠነ ሰፊ የማህበረ ኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞችን ያካተተ የአምስት አመት የትራንስፎርሜሽን እቅድ ነድፎ መተግበር ከጀመረ እነሆ ሁለተኛ አመቱን አገባድዷል።

መንግስት የአገሪቱን አጠቃላይ ገፅታ ለመለወጥ እያደረገ ባለው እንቅስቃሴም ባለፉት ስምንት አመታት በአገሪቱ ባለሁለት አሀዝ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ተከታታይ በሆነ ሁኔታ ሊመዘገብ ችሏል።ይህም በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ እየተደረገ ላለው የትራንስፎርሜሽን እቅድ ስኬታማነት ምቹ መደላድልን ፈጥሯል።

ይሁን እንጂ  የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ የአገሪቱን የህዳሴ ጉዞ ለማስቀጠል በጋራ እያደረጉ ያሉት ጥረት ያስመዘገበው ውጤት ያለፈበት መንገድ ግን እንዲሁ አልጋ በአልጋ በሆነ ሰላማዊ ሁኔታ የተገኘ አልነበረም ።

ዛሬ ኢትዮጵያን የመኀብኘት እድል ያገኘ ማንኛውም የውጭ ዜጋን በአድናቆትና በአግራሞት የሚመስጠው የአገሪቱ የኢኮኖሚ የፖለቲካውና የማህበራዊ ድሎችን ሟርተኞቹ ገና ከጅምሩ ለማክሸፍ ያልሸረቡት ያልወጡት አቀበትና ተራራ ያልሸረቡት ተንኮልና ያልጠነሰሱት ሴራ አልነበረም።

ምንም እንኳን ይህ የጥፋት ተግባር የኢትዮጵያን ህዝብና መንግስት ከተያያዙት የልማት ጉዞ ለአንዳች ደቂቃ ፈቀቅ ሊያደርጋቸው ያልቻለ ቢሆንም።

ሟርተኞቹ ከዛሬ ሃያ አንድ አመት በፊት ጀምሮ ስናውቃቸው የኢትዮጵያና ህዝቦቿ ቀጣይ ህልውና ከስልጣን ጥማቸው በልጦ ለአፍታም አሳስቧቸው አያውቅም።

ከእነዚህ ሃይሎች አብዛኞቹ በህዝብ ልጆች እልህ አስጨራሽ ትግል የተገረሰሰው የደርግ ስርአት ባለሟሎች የነበሩ እንደመሆናቸው የህዝብ ፍላጎትና ጥቅምን አጤነው እንቅስቃሴያቸውን በዚህ መንገድ ለመቃኘት መሞከር እንዴያውም አልፈጠረባቸውም።

የአመፅ ሃይሎቹ ለደርግ ስርአት ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አንበረከክም ያሉትን ጨምሮ ከስርአት አመለካከት ወጣ ያለ አስተሳሰብ ያላቸውን በርካታ ኢትዮጵያውያንን ዜጎች የጨፈጨፉ አምባገነኖች ናቸው።

አጠቃላይ የጥፋት እንቅስቃሴያቸውን በትእግስትና በትዝብት እየተከታተላቸው ያለው የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስትን ዝምታ እንደ ሞኝነት የቆጠሩት እነዚህ ፀረ ሰላም ሃይሎች "በለው፣ ቁርጠውና ፍለጠው" በሚል ርእዮተ አለም እየተመሩ የበርካታ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ህይወትን እንደዋዛ የቀጠፉም ናቸው።

ኢትዮጵያውያን ዜጎች በገዛ አገራቸው በሰላም መኖርና መንቀሳቀስ እንዲሁም በነፃነት ሃሳባቸውንና አመለካከታቸውን ያለማንም ተፅእኖ በሰላም ማራመድ አቅቷቸው የስርአቱ ባለሚል በነበሩት ጨቋኞች ግፍና የአገዛዝ ቀንበር ተማርረው ለስደትና ለመከራ የተዳረጉበት ሁኔታም እነርሱ እንደሚያስቡት በሰላም ወዳድ ኢትዮጵያዊ አእምሮ ከቶውንም የተረሳ አይደለም።

ይሁን እንጂ ሰላም ወዳጹና ትእግስተኛው የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ያለፈ የድህነት ታሪካቸውን በመቀየር የበለፀገች አገር ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ የሰነቁት ራእይ የሚጠይቀው የተቀናጀ ጥረት መላውን ዜጋ በአገሪቱ የማህበረ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካው መስክ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን በቁርጠኝነት መስራትን የሚጠይቅ በመሆኑ የሚርተኞችን የቂም በቀልና የንትርክ አጀንዳ ምእራፍ ዘግተው መላ ትኩረታቸውን ወደ ሰላምና ልማቱ አደረጉ።

እነዚህ የአመፅ ሃይሎችም በትናንት ስህተታቸውና ጥፋታቸው ተፀፅተውና ትምህርት ወስደው እነርሱም በአገሪቱ እየተካሄደ ባለው የሰላም የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደርጉ ይሆናል ከሚል እሳቤም ሁኔታዎችን መንግስትና ህዝብ ተረጋግተው በጥሞና ማስተዋል ጀመሩ።

ይሁን እንጂ እነርሱ ግን ካለፈ የወንጀል ድርጊታቸው አንዳችም ትምህርት ሳይወስዱ ዛሬም ሌላ አመፅና ጥፋት ከመደገስ የተቆጠቡበት ሁኔታ ከቶውንም አልተስተዋለም።

እንደሚታወቀው የደርግ ስርአት በህዝብ ልጆች መራር ትግል ተገርስሶ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ስርአት ከተመሰረተ በሁዋላ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች በኢትዮጵያ ታሪክ

ለመጀመሪያ ጊዜ የሚተዳደሩበትን ህገ መንግስት በጋራ ስምምነት ማፅደቃቸው ይታወሳል።

በዚህ ወቅት ታድያ ሚርተኞቹ የህዝቦችን መገነጣጠል የሚፈቅድ ህገ መንግስት በስራ ላይ ዋለ በሚል የበሬ ወለደ ተረት ፈጥረውና ፈብርከው ራሳቸውን አደናግረው በአገር ውስጥና በውጭ አገራት የሚኖረውን ዜጋ ጭምር በሀሰት ፈጠራቸው ማደናገርን እንደ ትልቅ ተግባር ተሰማሩበት።

የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በደርግ ስርአት የብሄር የቋንቋና የእምነት ልዩነታቸው ተደፍጥጦና ማንነታቸው ተጨፍልቆ በአኸዳዊ ስርአት ስር ሲተዳደሩ የነበረበት ሁኔታ አብቅቶ የፌዴራላዊ ስርአት በአገሪቱ ተግባራዊ ከሆነ በሁዋላ ዜጎች በማንነታቸው ኮርተውና ተከብረው በቋንቋቸው የመማርና የመዳኘት እንዲሁም በነፃ የመደራጀት ሃሳባቸውንና እምነታቸውን እንዲሁ በነፃነት የማራመድ መብት ተጎናፅፈዋል ።

ይሁን እንጂ እነዚህ የአመፅ ሃይሎች በኢትዮጵያ የፌዴራላዊ ስርአቱ ተግባራዊ በመሆኑ "ይህች አገር አበቀላት አከተመላት። ህዝቦቿም እርስ በእርስ ተጨራረሱ " እያሉ ሲያሟርቱ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው ።

ሟርታቸውም ሳይሳካ ህልማቸውም ሳይሰምር የኢትዮጵያም ህዝብ ጆሮውን ሳይሰጣቸው ይህው ድፍን ሃያ አንድ አመት አስቆጠሩ።

ሆኖም ግን እስካሁን ተስፋ ያልቆረጡት የጥፋት ሃይሎች በተለያዩ ጊዜና ወቅት ህዝብና መንግስትን ያቃቅራሉ ያሏቸውን ርእሰ ጉዳዮች እያነፈነፉ "የብጥብጥ ያለህ" ያላሉበት ጊዜ የለም ሊሳካላቸው አልቻለም እንጂ።

ይልቁንም እነርሱ ከሚመኙትና ከሚያልሙት በተቃራኒ ኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሰላምና መረጋጋቷ እየጎለበተ፣ የብሄር ብሄረሰቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት እየተጠናከረና ኢኮኖሚዋም በፍጥነትና በተከታታይ እያደነገና እየተመነደገ የሚታይባት አገር ሆናለች።

አገሪቱ በሁሉም መስክ እያስመዘገበችው የምትገኘው ይህ አስደናቂ ለውጥና እድገት የተገኘው ግን እንዲሁ በዋዛ ሳይሆን መንግስት አገሪቱን ወደፊት ለማራመድ የነደፋቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ህዝቡ በጥንካሬና በታታሪነት ተግባራዊ በማድረጉ ነው።

ይህም ህዝቡ በመንግስት ላይ ያለው አመኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ መምጣቱን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ሲሆን በተቃራኒው የአመፅ ሃይሎች ደግሞ እየተከተሉት ባለው የአመፅና የብጥብጥ ስልት በህዝቡ እንዲተፉ አድርጓቸዋል። በተለይም የ2002 አገርዓቀፍ ምርጫ ውጤት ይህን ሃቅ በመጀመሪያ ለእነርሱ ቀጥሎም ለአለምዓቀፉ ማህበረሰብ አረጋግጦ ያለፈ መሆኑ አንድ ማሳያ ነው።

እነዚህ የአመፅ ሃይሎች የእነርሱ የአመፅና የብጥብጥ ስልት ልማቷ እየተፋጠነ ሰላም ልማትና ዴሞክራሲዋን ይበልጥ እያጎለበተችና በዚህ ረገድ በአፍሪካ በአርአያነቷ ተጠቃሽ እየሆነች በመጣችው በኢትዮጵያ ምድር ዘንድ ሊሳካላቸው እንደማይችል ቢገነዘቡትም ቅሉ እውነታውን የሚቀበሉበት ህሊና ግን አልተፈጠረባቸውም።

በመሆኑም ከአመት አመት የአመፅና የጥፋት ስትራቴጂያቸውን በአገሪቱ ላይ የሚያሳካላቸው የመሰላቸውን ርእሰ ጉዳይ ሁሉ እንደ ውሻ እያነፈነፉ ከማላዘን የተቆጠቡበት አንዳችም ጊዜ አልታዬም።

ሟርተኞቹ እንዴያውም ከቅርብ አመታት ወዲህ የለየለት የአመፅና የብጥብጥ ፍቅራቸው በአጋፋሪያቸው ግንቦት ሰባት በኩል ከአተራማሹ ሻእቢያ ጋር ጋብቻ እንዲፈፅሙ አስገድዷቸዋል።

እንደሚታወቀው ግንቦት ሰባት የተሰኘው የለየለት ፀረ ሰላምና አሸባሪ ሃይል የአብራኩ ክፋይ ከሆነው ራሱን የአርበኞች ግንባር ብሎ ከሚጠራውና አነግ ከተሰኘው የአንድ ጎልማሳ ሰው እድሜ ሲያስቆጥር እየተንኮታኮተ ህልውናው ከመቅሰሙ በስተቀር ለኦሮሞ ህዝብ አንዳች ካልፈየደው ድርጅት ጋር ግንባር ፈጥረው ሻእቢያን አቤት ወዴት የሚሉት ተላላኪዎች ሆነዋል።

እነዚህ የአመፅ ሃይሎች የኢትዮጵያ ህዝብ ለረዥም ጊዜ ከአምባገነኖች ጋር ባካሄደው ትግል የተጎናፀፈውን ሰላምና ዴሞክራሲ በማጨናገፍ ከልማቱ ሊያስተጓጉሉት ከሻእቢያ ጋር በመሆን ላይ ታች ቢሉም በተቀናጀ የህዝቡ ጥረት ይህው ሰይጣናዊ ድርጊታቸው ከምኞት አልዘል ብሏቸው በሚርታቸው ብቻ ሊቀጥሉ ተገደዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህን ፀረ ሰላም ሃይሎች እየተከታተለ እኩይ ድርጊታቸውን በማጋለጥ ተላላኪዎቻቸውም በቁጥጥር ስር ውለው በህግ ከለላ ስር ተገቢውን ቅጣታቸውን እንዲያገኙም እያደረገ ይገኛል።

በዚህም አገሪቷ በተረጋጋ ሰላሟ ላለፉት ሃያ አንድ አመታት ያስመዘገበችውን ዙሪያ መለስ አንፀባራቂ ድል ይበልጥ በተጠናከረ ሁኔታ በህዳሴ ጉዞዋ በማስቀጠል ሂደት ላይ ትገኛለች።

የኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞ አገሪቱ በአጠቃላይ ሰላሟ መረጋጋቷና ኢኮኖሚያዊ እድገቷ በምስራቅ አፍሪካ የነበራትን ታሪካዊ ስፍራ እንደቀየረው ከአንድ ወር በፊት በአይጋ ፎረም ድረ ገፅ Josh Maiyo በተሰኙ በUniversity of Leeds, UK and VU University Amsterdam የPhD researcher የየሰፈረውን ፅሁፍ እንዳስታውስ አድርጎኛል።

እኚሁ Josh Maiyo የተሰኙት ተመራማሪ የዑጋንዳ የቀድሞ ጋዜጠኛ የሆነው ቻርለስ ኦንያንጎ-ኦቦ በምስራቅ አፍሪካ የመልክአ ምድራዊ ፖለቲካ ውስጥ ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ የሚለውጡ ሦስት ጂኦ ፖለቲካዊ ጉዳዮች መከሰታቸውን በመግለፅ ከእርሳቸው በፊት ያወጣው የትንታኔ ፅሁፍ ሃሳብ ላይ ሙሉ በሙሉ እንደሚስማሙበት በመግለፅ ፅሁፋቸውን ይጀምራሉ።

ይህም የምስራቅ አፍሪካ 'የኃይል ሚዛን ' መሪ ከነበሩ የቀድሞ አገራት (ኬንያ፣ዑጋንዳ እና ታንዛኒያ) ማኅበረሰቡን ዘግይታ ወደ ተቀላቀለችውና በአሁኑ ወቅት የቀጣናው ወታደራዊ እና ኢኮኖሚ መሪ ወደ ሆነችው ኢትዮጵያ በእርግጥም ተዛውሯል ይላሉ።

አስከትለውም ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በሶማሊያ ማረጋጋትና በአጠቃላይም ደቡብ ሱዳንን ጨምሮ በአካባቢው የፀጥታ ጉዳዮች ላይ እየተጫወተች ባለው ሚናና ኬንያን ጨምሮ ለአካባቢው የምስራቅ አፍሪካ አገራት የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ማለትም የኤሌክትሪክ ሃይል በማዳረስ ረገድ ኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር እያደረገች ባለችው አስተዋፅኦ ጭምር የሚገለፅ መሆኑንም ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ ሚርተኞች እንደተመኙላት ሳይሆን ህዝቦቿና መንግስት ለተግባራዊነቱ እየተጉለት የሚገኘውን መካከለኛ ገቢ ወዳላቸው አገራት ተርታ የመሰለፍ ራእይዋን

በጥቂት አመታት ውስጥ ለማሳካት ትችላለች የሚል እምነት ላይ እየደረሱ ያሉት በአሁኑ ወቅት ጥቂት የሚባሉ አይደሉም።

የበርካታ ብሄር ብሄረሰቦችና የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎችና እምነት ተከታዮች አገር የሆነችው ኢትዮጵያ ባለፉት ሃያ አንድ አመታት ተግባራዊ ያደረገችው የፌዴራላዊ ስርአቷ ሚርተኞቹ እንደተመኙት

ሳይበታትናት ይልቁንም ዴሞክራሲያዊ አንድነቷን አጠናክሮላታል።ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ የመጣው ሰላሟና መረጋጋቷም ከአፍሪካ አገራት በአርአያነት ተጠቃሽ እንድትሆን አድርጓታል።

ይህም ላለፉት ስምንት አመታት ካስመዘገበችው የኢኮኖሚ እድገት በተጨማሪ በሚቀጥሉት አምስት አመታትም ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት ከሚያስመዘግቡ ሶስት ቀዳሚ አገራት መካከል ከቻይናና ህንድ ቀጥሎ በሶስተኝነት ደረጃ እንድትገኝ አስችሏታል።

አገራችን ይህ በኢኮኖሚ በማህበራዊና በፖለቲካዊ መስክ እያስመዘገበች ያለው ፈጣንና አስደናቂ መሻሻልና እድገት ደግሞ እያገባደድነው ባለው አመት ብቻ ገፅታዋን በመቀየር ለህዝቦቿ መለወጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸውን ሶስት ትላልቅ ጉባኤዎች የማስተናገድ ብቃት ያላት አገር መሆኗን አለምዓቀፉ ማህበረሰብ ተገንዝቦ እንዲመርጣት አስችሎታል።

አለምዓቀፉ ማህበረሰብ አገራችን ቀድሞ የምትታወቅበትን ገፅታዋን በመቀየር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸውን ኢካሳን የአለም ኢኮኖሚክ ፎረምና የመሳሰሉ በርካታ የአለም አገራት ተወካዮች የተሳተፉበትን ትላልቅ አለምዓቀፍ ጉባኤዎች በህዝቦቿና መንግስት የጋራ ጥረት የማስተናገድ ታሪካዊ ሃላፊነቷን በብቃት ተወጥታለች።

በዚሁ ወቅት በአዲስ አበባ በእንግሊዝኛ ከሚታተሙ ጋዜጦች ፎርቹንና ካፒታል የተሰኙት ከእንግዶች ጋር ያካሄዱትን ቃለ ምልልስ ዋቢ አድርገው እንደዘገቡት ከሆነ በአዲስ አበባ እየተገነቡ ያሉት ትላልቅ ሕንፃዎችና በአጠቃላይ በመዲናዋ ያለው የኢንቨስትመንትና የንግድ እድል በ22ኛው የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም ጉባዔ ተሳታፊዎች ዘንድ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መነቃቃት ብሎም ለአገሪቱ ሕዳሴና መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ ለመሰለፍ ላላት ፍላጎት እንደ ምልክት ተወስደዋል ሲሉ ነበር ያሰፈሩት።

በአሁኑ ወቅት የአመፀኛውና የፀረ ሰላም ሃይሉ ሚርት የህዳሴ ጉዞዋን ለአፍታም ሳይገታው የቀድሞ አሉታዊ ገፅታዋን እየቀየረች በእድገቷ በሰላምና መረጋጋቷ መታወቅ የጀመረችው አገራችን በአንፀባራቂ ግስጋሴዋ እየቀጠለች ትገኛለች ።ያለፉት ሃያ አንድ አመታት የሰላም የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ጉዞዋም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነውና ።

እደተለመደው ውሾቹ ይጮሃሉ ግመሎቹ ግን ጉዟቸውን ለአፍታም ሳይገቱ ቀጥለዋልና።